የዓሲምባ ፍቅር

ደራሲ፣ ካሕሳይ ኣብራሃ ብስራት/አማኑኤል

ሃያሲ፣ በየነ/ጉራ ገብራይ፣ btesfu45@gmail.com

*ደንማርክ*

## ማን ያውራ የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ

የኢትዮጵያ ህዝባዊ አቢዮታዊ ሰራዊት/ኢህአሰ በ1967 ዓ.ም. አጋማሽ ትጥቅ ትግሉን በትግራይ ጀምሮ በ1985 ዓ.ም. በጎንደር/ቋራ በህወሓት/ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ የተመታና ዛሬ ታሪክ ብቻ ሆኖ የቀረ ሰራዊት ነው። እኔ እስከማውቀው ስለ ኢህአሰ እስካሁን በመጽሓፍ ደረጃ የጻፉት ጓድ አሰማማውና ጓድ ካሕሳይ/አማኑኤል ማንጁስ ብቻ ናቸው። ጓድ አስማማው የጻፈው መጽሓፍ አግኝቼ ስላላነበብኩት ስለ ኢህአሰ መጻፍ ያለበት ገና ብዙ የተደበቀና ያልተደረሰ ታሪክ ሰፊ ስለሆነ በጀመርከው ቀጥልበት ከማለት ውጭ ለጊዜው የምለው የለኝም። የጓድ አማኑኤል ማንጁስ የዓሲምባ ፍቅርን ግን አግኝቼ ስላነበብኩት፣ ስለ መጽሓፉ ደራሲ፣ የመጽሓፉ ይዘትና ደራሲውን አስታከው በኢህአሰና ህወሓት የ1970 የትግራይ ጦርነት ወቅት ትግራዊያን ጓዶችን እንደ ከሃዲዎችና የህወሓት ሰላዮች አስመስለው በትችት ስም ከቀረቡት የውሸት ውንጀላዎች ውስጥ መልስ ያስፈልጋቸዋል ላልኩዋቸው በቀደም ተከተል መልስ እሰጣለሁ።

ከዛ በፊት ግን ጓድ አማኑኤል ማንጁስ የዓሲምባ ፍቅርን በመጻፉ እስከ ዛሬ አጥቸው የነበረ ጉልበትና ድፍረት ስለሰጠኝ ጓዱን ከልብ እያመሰገንኩ፣ በትግሉ ሜዳ ለ18 ዓመታት ከቆየ በኋላ ዛሬ ታሪክ ሆኖ ስለቀረው ኢህአሰ፣ ያልተነገረ/ያልተጻፈ ታሪክ በትክክል እንዲጻፍና እንዲታወቅ፣ በሰራዊቱ ውስጥ የነበረን አባላት አተኩረንባቸው የምናውቀውን ከስሜትና ከግል ፍላጎት ርቀን ሀቁን ብቻ ብንጽፍበት መልካም ነው የምላቸውን አከባቢዎች፣ ለናሙና ያህል አንዳንድ የማስታውሳቸው ክንዋኔዎችን እየጠቀስኩ ለማስቀመጥ እፈልጋለሁ።

የኢህአፓ/ሰ አመራር ሁሉም ነገር በሚስጥር የሚሰራ የነበረ/የሆነ ድርጅት ስለነበረ/ስለሆነ የኢህአፓ/ሰ የተሟላ ታሪክ ለመጻፍ ከሁሉም በላይ ሀላፊነቱ የሚወድቀው ከከፍተኛ አመራር እስከ ታችኛው አመራር ድረስ በአመራር ላይ የነበሩ፣ ዛሬ የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው ዝምታን መርጠው ቁጭ ብለው ያሉ ጓዶች ላይ መሆኑ ጥርጥር ባይኖረውም፣ ሁላችን እንደ ጓድ አማኑኤል እና ጓድ አስማማው ዓይነቶቹ በራስ አነሳሽነትና አፍላቂነት የምናውቀው ብንጽፍ የነዛ ሰማዕታት ምንነትና ታሪክ በትክክል በማሳወቅና ስለ ኢህአፓ/ሰ ሀቁን ለማወቅ ለሚፈልግ የኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ውለታ እንደምንውልለት ምንም ጥርጥር የለውም። በተለይ ኢህአፓ/ሰ ምን ዓይንት ድርጅት እንደነበረ ከኢህአፓ/ሰ ጠላቶች ብቻ እየተነገረው ያደገና አሁንም እያደገ ላለው ወጣቱ ትውልድ ትክክለኛ የኢህአፓ/ሰ ታሪክ ከራሳቸው ከባለታሪኮቹ እንዲያውቅ ማድረግ የኛ የኢህአፓ/ሰ አባላት የነበርንና አሁንም ነን የሚሉ ሃላፊነትና ግዴታ መሆኑም መዘንጋት የለበትም። ስለሆነም ታሪካችን ሳይበረዝ በትክክል እንዲመዘገብ የምንፈልግ፣ ልንገናኝ የምንችል እየተገናኘን በቡድን፣ ይህ ዓይንት ዕድል የሌነን ደግሞ በግልም ቢሆን በሚቀጥሎት አከባቢዎች አተኩረን ብንጽፍ የተሟላ የኢህአሰ ታሪክ ለመጻፍ መልካም ጅማሮ ይሆናል እላለሁ።

**ሀ. ለወደፊት በሚጻፈው የኢህአሰ ታሪክ ቱክረት ሊሰጥባቸውና ሊጻፍባቸው የሚገቡ አከባቢዎች/areas**

- ኢ.ህአሰ 1967 _ 1985 የ18 ዓመት በትጥቅ ትግሉ ቆይታው በትግራይ በዓጋመ፣ ክልተ አውላዕሎ፣ ምስራቃዊ ዓድዋ ገጠራማ ክፍሎች ከጠላት አጽድቶ የመንቀሳቀሻ ወረዳውን አድርጎ የተንቀሳቀሰ፣ ህዝባዊ መዋቅሮችን ዘርግቶ የነበረና በህዝብም ጥሩ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ሰራዊት ነበር። በጎንደር ክፍለሀገርም በጸለምት፣ በበለሳ፣ በቆላወገራ፣ በአርማጭሆና በቋራ ወረዳዎች ሰፋፊ ወረዳዎችን ከጠላት ነጻ በማውጣት የተንቀሳቀሰ፣ ህዝባዊ መዋቅሮችን ዘርግቶ በህዝቡም ተቀባይነት አግኝቶ የነበር ሰራዊት ነበር። ኢ.ህአሰ በትግራይ ሆነ በጎንደር በተለያዩ ከተሞች በርካታ ወታደራዊ ኦፐሬሽኖችን በማድረግ በርካታ ድሎችንም አስመዝግቧል። ኢ.ህአሰ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችን ከጫፍ እስከ ጫፍ አንድ ላይ አሳትፎ ያታገለ፣ ከተሜውንና ገበሬውን ሁሉ ያቀፈ፣ ዴሞክራሲያዊትና ሉዓላዊት ኢትዮጵያ እንድትመሰረት ለሚደረገው ትግል ውድ ህይወታቸውን ለመስጠት ምንም ወደኋላ በማይሉ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች የተገነባ ሰራዊትም ነበር። ይህን ክቡር ዓላማ ይዞ የተነሳ ሰራዊት፣ ይህን ዓላማን እግቡ ለማድረስ በሚደረገው ትግል የሚከፈለውን መስዋዕትነት ለመክፈል ምንም ወደኋላ የማይሉ አባላት የነበሩት ሰራዊት፣ የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል ከሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች በቀላሉ ለማግኘት ችግር ያለነበረው ሰራዊት፣ በተንቀሳቀሰበት አከባቢ ሁሉ ህዝባዊ ድጋፍ ያልተለየው ሰራዊት...ወዘተ. ለምን ከ18 ዓመት የትግል ጉዞ በኋላ ታሪክ ሆኖ ቀረ? ለኢ.ህአፓ/ሰ ውድቀት መሰረታዊ ችግሩ ምንና የቱ ላይ ነበር? ኢ.ህአሰን እንደዚህ ታሪክ ሆኖ እንዲቀር በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ጠላቶች የተሰነዘረበት ዱላ እንዳለ ሆኖ የራሱ በድርጅቱ ውስጥ በተለያየ ጊዜ የተከሰቱ የውስጥ ችግሮች ሚናስ ምን ነበር? የሚሉ ጥያቄዎች ገና በስፋት ተጠንተውና ተመርምረው ተገቢ መልስ ማግኘት ያለባቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ናቸው።
- የኢ.ህአሰ ከ1967_1970 ዓ.ም. የትግራይ ቆይታና እንቅስቃሴ ራሱ ከአንድ መጽሓፍ በላይ ሊጻፍባቸው የሚችሉ በርካታ ክንዋኔዎች ተከናውነዋል፣ ትግራይ የነበረው ሰራዊት በዚህ አጭር ጊዜ ብዙ ፈተናዎችም ገጥመውታል። ለመጥቀስ ያህል፣ የ1969 የደርግ የቀይ ሽብር እወጃና እርምጃ ያስከተለው የአዲስ መጪዎች ጎርፍ የትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን እንደ አንድ ጉሪላ ሃይል ደረጃውን ጠብቆ ለማደግ አለመቻል፣ ባዲስ መጭዎችና በነባሮቹ አባላት መካከል የተፈጠረው የወታደራዊ ዲሰፕልንና አሰራር ልዩነት፣ ይህን ልዩነት ለማረም በሚል በአዲስ መጪዎች የሞብ እንቅስቃሴ የተገፋው እርማት እንቅስቃሴና አሉታዊ ውጤቱ፣ በሰራዊቱ ውስጥ አንጃ ተፈጠረ ተብሎ የተካሄደው እንቅስቃሴና ውጤቱ፣ የኢ.ህአሰና ህወሓት ከጅምሩ ጀምሮ የነበረው መጥፎ ግኑኝነት ወደ ጦርነት አድጎ የተካሄደው ጦርነትና ፍጻሜው...ወዘተ በርግጥ በዓሲምባ ፍቅር ውስጥ አልፎ አልፎ በተወሰነ ደረጃ የተጠቀሱ ቢሆንም ገና ብዙ ሊጻፍበት የሚገባ አከባቢ ነው።

- ትጥቅ ትግሉን በጎንደር/ጸለምት ለመጀመር በ1968 የተንቀሳቀሱት ሁለት ጋንታዎች የመጀመሪያ የጸለምት እንቅስቃሴ ራሱን የቻለ መጽሓፍ ሊጻፍበት የሚገባ ሌላ አከባቢ ነው። እነዚህ ሁለት ጋንታዎች ገና ጸለምት እንደገቡ ልክ ወሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ገብተው በገሬው የከበባ ጦርነት ጠፍተው እንደቀሩ ጋንታዎች ዓይነት ህዝባዊ ከበባዎችና ጦርነቶች በተከታታይ ገጥሞአቸዋል። ተከታታይ ከበባዎችን እንዴት አክሽፈው/አሸንፈው የጸለምትን ወረዳ እንዴት እንደተቆጣጠሩትና ጸለምት የኢ.ህአሰ ማሳባሰቢያ ማእከል ሆኖ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግል እንዳስቻሉት ራሱን ችሎ በሰፊፍ መተረክ ያለበት ራሱን የቻለ ሌላ አከባቢ ነው።
- ከትግራይ በኤርትራ በኩል ያፈገፈገውና በኤርትራ ለ5 ወራት ያህል የቆየው ሰራዊት ተከዜን ተሻግሮ፣ ወልቃይትን አቋርጦ ጸለምት የደረሰው በ1971 መባቻ ነበር። ይህ ሰራዊት ጸለምት ሲደርስ ጸለምት የነበረው ሰራዊት ላይ ደርግ ከበባ አውጆ የጸለምት ጦርነት ውስጥ ሆኖ ነበር። በከበባው እነ

ማይጸምሪ፣ ዓዲ አርቃይ፣ ሀዋዛ የመሳሰሉ ከደርግ ነጻ ወጥተው የነበሩ ከተሞች እንደገና በደርግ የተይዘው ደርግ ወደ ማኽል ጸልምት እየገፋ የነበረበት ሁኔታ ላይ ነው ከኤርትራ ያፈገፈገው ሰራዊት ጸለምት የደረሰው። ከኤርትራ የፈገፈገው ሰራዊት ገና ከነበረበት ሁኔታ ገና ሳያገመግም በዚህ ከባባ ወስጥ መግባት ራሱን የቻለ ችግር ነበረው። ደርግ ወደ ማኽል ጸለምት እየገፋ እያለ የድርጅቱ አመራር ሰራዊቱን ወደ 4 ሪጅኖች በመከፋፈል 4 ሪጅኖች በ1971 ላይ ተመሰረቱ። 4ቱ ሪጅኖችም፣ ሪጅን 1 ጸለምት፣ ሪጅን 2 አርማጭሆ፣ ሪጅን 3 በለሳ፣ ሪጅን 4 ቀላወገራ/ወልቃይት ነበሩ። እያንዳንዱ ሪጅን 3 ሃይሎችና ራሱን የቻለ የሪጅን አመራር ነበረው። የሰራዊቱ ጠቅላይ አመራርና በወቅቱ ሜዳ የተሰባሰበው የድርጅቱ ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት እንዳሉ ተጠቃልለው ወደ ሪጅን 2 ከሄደው ሰራዊት ጋር ነበር የሄዱት። እነዚህ አራት ሪጅኖች ከአንድ ዓመት የተናጠል እንቅስቃሴ በኋላ በኢህአፓ/ሰ ብተና እየተባለ በሚታወቅ እንቅስቃሴ ህልውናቸው አከተመ። እነዚህ አራት ሪጅኖች በየሪጅናቸው ያደረጉዋቸው እንቅስቃሴዎች፣ በየሪጅኑ ይህ ብተና የሚባለው እንቅስቃሴ ምን ይመስል እንደነበረ፣ ...የየሪጅኑ ትክክለኛ ሁኔታ የሚታይበት ራሱን ችሎ መጻፍ ያለበት ይሆናል። ሌላ በሪጅን 3 የአባላት ብተና ከሌሎች ሪጂኖች ለየት ያለ ክስተት ተከስቶ ነበር። የተወሰኑ ወደ ከተሞች ሲገቡ፣ በጣም ጥቂት ደግሞ ወደ ጸለምት በመምጣት ጸለምት የነበሩ አባላትን ሲቀላቀሉ፣ የማይናቅ ቁጥር ያለው አንድ ቡድን ተደራጅቶ ከነበው መሳሪያ የተመረጠውን ይዞ ወደ ትግራይ በመሄድ በህወሓት ድጋፍ የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ኢህዴን በሚል ተደራጅቶ ከህወሓት ስር ትግሉን ቀጠለ።

- ብተና እየተባለ የሚታወቀው ራሱ በሰፊው መጠናትና መመርመር ያለበት ሌላ እጅግ ውስብስብ አከባቢ ነው። አንድ ድርጅት/ሰራዊት ከነበሩት አመራሩ ሆነ አባላቱ ብዙሃኑ ጥለውት ሄደው ውሁዳኑ ብቻ የቀረቡት ሁኔታ እንዴትና ለምን ተፈጠረ? ያ ሁሉ አባል ኡነት እንደሚባለው በተወሰኑ በታኞች በሚባሉ ግለሰቦች ስብከትና ፕሮፓጋንዳ ነው የተበተነው ወይስ ችግሩ ሌላ ነው? ኡነት ያ ሁሉ ታጋይ የትግሉን ውጣ ውረድ ለመቋቋም ስላልቻለ ነው እንደዛ የተበተነው? .... ወዘተ. የመሳሰሉ ጥያቄዎች በሰፊት ተጠንተው መመለስ ያለባቸው ናቸው። በዚህ በብተና ዙሪያ በሚደረገው ጥናት ሆነ ትክክለኛ ታሪክ መጻፍ ላይ አሁንም ይበልጥ ሃላፊነቱ የሚወድቀው በአመራር የነበሩና በህይወት የተረፉ ጓዶች ላይ ቢሆንም እያንዳንዳችንም ቢሆን ስለ ሁኔታው የምናውቀውን በመጻፍ በኩል ግዴታችን ልንወጣ እንደሚገባን መታወቅ ያለበት ይመስለኛል።
- ብተና እየተባለ በሚታወቀው የኢህአፓ/ሰ አብዝሃ አመራሩና በርካታ አባላቱ ድርጅቱን ለቀው ከሄዱ በኋላ፣ ሪጅን 2፣ ሪጅን 3ና ሪጅን 4 እንዳሉ ታጠፉ። ሪጅን 1/ጸለምት ከሪጅን 3ና ሪጅን 4 የተረፉትን አባላት ጨምሮ በድጋሚ ሜዳ የቀረው ኢህአሰ ማሰባሰቢያ ሆነ። በወቅቱ በጸለምት በተሰራው ድርጅታዊ ስራ በርካታ አርሶ አደሮች ጓዶች ወደ ሰራዊቱ መቀላቀል ጀምረው ስለነበረ እነዚህ ከሪጅን 1፣ ሪጅን3 እና ሪጅን 4 ከብተና ተርፈው በጸለምት የተሰባሰቡት አባላት የጸለምት አርሶ አደር ጓዶችን በመያዝ እንዳዲስ በመዋቀር በጸለምት እንቅስቃሴአቸውን ቀጠሉ። አብዛኛው አባል ድርጅቱን ለቆ መሄዱን የተረዳ ደርግ ጸለምት በቀረው ኢህአሰ ላይ አጠቃላይና ተከታታይ ከበባ በማድረጉ ከብተና በኋላ በጸለምት የቀረው ትንሽ ሰራዊት በጸለምት ትግሉን የመቀጠል ዕድሉ አከተመ። በዚህ ጊዜ አመራሩና በሰራዊቱ ውስጥ የነበሩ ሲኒየር አባላት ከንግዲህ በጸለምት አሁን ባለን ሀይል ትግሉን መቀጠል ስለማንችል ቀላ ወገራን አቋርጠን ወደ ሪጅን 2 እንሂድና ከሪጅን 2 ጓዶች ጋር ተቀላቅለን ትግሉን በሪጅን 2 በኩል ሱዳንን ጀርባችን አድርገን እንቀጥል የሚለውን ወስነው ወደ ሪጅን 2 ለመንቀሳቀስ ዝግጅት ተጀመረ። ዝግጅቱ ተጠናቀ ወደ ቀላ ወገራ እንቅስቃሴ ለመጀመር ከደጋ ጸለምት ሙሉ በሙሉ አፈግፍገው ወደ ቀላ ጸለምት ብራ ዋሲያ እንደደረሱ የሪጅን

2 ጓዶች ወደ ሱዳን ጠቅልለው መግባታቸውን የሚያውቅ የነበረ አቶ መርሻ ይህን መርዶ ለሰራዊቱ አመራር አረዳ። የሰራዊቱ አመራርም ይህን ሉብቻችን በምስጥር ይዘን መቀጠል ስለማንችል ሲንየር አባላትን ስለ ጉዳዩ ማማከርና ጓዶቹ ምን እንደሚወስኑም ከነሱ ጋር መምከር አለብን ብለው ሲኒየር አባላትን አሰባስበው ስለ ሪጅን 2 ጓዶች ጠቅልለው ወደ ሱዳን መግባትና ሪጅን 2 የሚባል አለመኖሩን ተናገሩ። የተሰባሰቡት ሲኒየር አባላት በጉዳዩ በስፋት ከተወያዩ በኋላ ትግሉን መቀጠል አለብን፣ ትግሉን እንዴትና የት ላይ መቀጠል አለብን የሚለውን ለመወሰን ግን ሰከን ብለን በጥልቀት ለመወያየት ጊዜና ቦታ ያስፈልገናልና ከጀብሃ ጋር በመነጋገር ጀብሃ ቦታ እንዲሰጠን ይጠየቅ በሚል ተስማሙ። ጀብሃዎችም እሺ ብለው ስለተስማሙ ሰራዊቱ ለሰፊ ውይይት ወደ ኤርትራ/በርቲያ ሄደ። በኤርትራ/በርቲያ በረሃ ወደ 5 ወር የፈጀ ሰፊ ውይይትና ክርክር እንዴትና የት ትግሉ መቀጠል አለበት በሚለው ሁሉንም አባላት ያሳተፈ ሰፊና ጥልቅ ሰሚናር ተካሄደ። ከዚህ 5 ወር ውይይት በኋላ አብዝሃው ትጥቅ ትግሉ በጎንደር መቀጠል እንዳለበት በመስማማት ወደ ጎንደር ሲመለሱ የተወሰኑ አባላት ወደ ጎንደር እንቅስቃሴ ሊጀመር ከቀናቶች በፊት በቡድን ከበርቲያ/ኤርትራ ወደ ሱዳን ወጡ። ይህ ከኤርትራ ወደ ጎንደር የተመለሰው ሰራዊት ጸለምት ሙሉ በሙሉ በደርግ ቁጥጥር ስር መልሶ ስለወደቀ፣ ወልቃይት ደግሞ በህወሓት ቁጥጥር ስር ስለነበረ በቀጥታ ወልቃይትን አቋርጦ ወደ ግጨው በረሃ ገባ። ግጨው በረሃን ማእከል በማድረግ በጸገዴና አርማጭሆ የተወሰነ እንቅስቃሴ ካደረገ በኋላ በተወሰኑ ከሰራዊቱ የከዱ አባላት ቢትወደድ አዳነና የተወሰኑ ሰዎቻቸው ከሱዳን ጠቅልለው ሀገር ቤት በመግባት ለመታገል መንገድ ላይ እያሉ ስለገደሉዋቸው የአርማጭሆና ጸገዴ ህዝብ ከአህአሰ ጋር የነበረው ግኑኝነት ተበላሸ። የአርማጭሆና የጸገዴ የኢዴህ አባላት የነበሩ አርባኞች ህዝቡን አስተባበረው ኢህአሰ ላይ ጦርነት ከፈቱ። በዚህ ጦርነትም ከኢህአሰ በኩል እነ ጓድ ሓዲሽ በየነ፣ ጓድ ደንጀር፣ ጓድ ጂጋር፣ ጓድ ዓብደላ፣ ጓድ ዮሃንስ ሞሽዳያን፣ ጓድ ካሕሳይ፣ ጓድ ጠዓመና....መሰሎቹ ጓዶች ተሰዉ። ከህዝቡ ወገንም በርካቶች ተሰዉ። ከዚህ ሁኔታ በኋላ ኢህአሰ ግጨውን ማእከል አድርጎ በአርማጭሆና በጸገዴ በኩል የሚደረገው ትግልና እንቅስቃሴ አከተመ። ስለሆነም ሰራዊቱ በጭልጋ በኩል አቋርጦ ወደ ቋራ በ1973 መጨረሻ ተሻገረ። ይህ ከበርቲያ/ኤርትራ እስከ ቋራ መግባት ያለው ሂደት ራሱ ችሎ በስፋት ሊመረመርና ሊጻፍበት የሚገባ ነው።

- ይህ ቋራ የገባው ሰራዊት ቋራን ማእከል በማድረግም እስከ 1985 አንቅስቀሴውን እስከ ጎጃም ድረስ አስፋፋ፣ በቋራና ዙሪያዋ ሰፊ አከባቢን ከጠላት ቁጥጥር ነጻ አወጣ፣ የሰራዊቱ ቁጥርም ወደ ባታሊዮኖች አድጎ ነበር፣ በርካታ ክፍልታትም ተመስርተው ነበር፣ ሰራዊቱንና በሱዳን የነበሩትን አባለቱን ሁሉ በፋይናስ ሊረዱ የምችሉ ሰፋፊ ራስን በራስ የመቻል ፕሮጀክቶችንም እስከ ማቋቋም አድጎ ነበር፣ ከቋራ በረሀ የሚሰራጭ ረዲዮ ጣቢያ እስከ መመስረትም ችሎ ነበር፣ የድርጅቱ መዋቅርም በጎንደርና በጎጃምም በበርካታ ወረዳዎች ዘርግቶ ነበር፣ ብዙውን የምዕራብ ጎንደር ቋራን የሚያወስኑ ወረዳዎችና እንዲሁም የተወሰኑ የጎጃም ወረዳችም ከጣላት ነጻ አውጥቶ መንቀሳቀሻ ወረዳዎቹን አድርጎ ነበር። ይህ የኢህአሰ ክፍል ከቋራ መግባት እስከ 1983 ያደረገው እንቅስቃሴ ራሱ ችሎ በሰፊው ሊተረክ የምችል ታሪክ ያለው ስለሆነ በዚህ እንቅስቃሴ ያለፉ ጓዶች ልያስቡበትና ሊጽፉበት ይሚገባ ራሱን የቻለ አከባቢ ነው።
- 1983 ግንቦት ከደረግ መውደቅ ማግስት ህወሓት/ኢህአዴግ ኢህአፓ/ሰ ላይ ሃይሉን አሰባስቦ ዘመቻ ከፈተ። በሱዳን የነበሩ የድርጅቱ ጸ/ቤቶችን ዘጋ፣ ንበረቶቹን እንዳለ ወረሰ፣ ሱዳን የነበሩ የድርጅቱ አባላት የስደተኝነት መብታቸውን በመንጠቅ የቁም እስረኞች እንዲሆኑ አደረገ። በርግጥ ህወሓት ኢህአዴግ ኢህአፓ/ሰ ላይ እንደሚዘምት አስቀድሞ ይታወቅ ነበር። ከዚህ አንጻር እንደተለመደው የድርጅቱ አማራርም በሚስጥር ዝግጅት ሊያድር እንደምችል ይገመት ነበር። ዝግጅቱ ኢህአሰ የቋራን

ህዝብ ይዞ የህወሓት/ኢህአዴግ ከበባን ይከላከላል የሚለው መሆኑ በሲኒየር አባላት ደረጃ የታወቀው ግን ልክ ጦርነቱ ሊጀመር አከባቢ ነበር። መካናይዝድ የሆነ ሰራዊት ይዞ የመንግስት ስልጣን ከተቆጣጠረ ሀይል ጋር ገና በሁለተኛ የጉሪላ ዕድገት ደረጃ ላይ ያለ ሰራዊት ይዘህ ፊት ለፊት እላተማለሁ ማለት አዋጭ እንዳልሆነ በግልጽ የታየበት ጦርነትም ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋራ ተጀመረ። ገና ጦርነቱ እንደተጀመረ ብዙ አባላት ተሰዉ፣ 4 የማእከላዊ ኮሚቴ አባላትና የተወሰኑ ሲኒየር አባላት ያለቡት ቡድን ገና በጦርነቱ መጀመሪያ ተማረኩ። አላጥሽ በሚበል በረሃ ላይ የነበረው ማእከላዊ ቤዝ በህወሓት ቁጥጥር ስር ወደቀ። በመቀጠልም ሰፊ የቋ አከባቢና ቋራ/ የቴድሮስ ከተማም በህወሓት ቁጥጥር ስር ወደቀ። ጦርነቱ እየቀጠለ እንደ ሄደም ብዙ አባላት እየከዱ ለህወሓት/ኢህአዴግ እጃቸውን መስጠት ጀመሩ። የተወሰኑም ወደ ሱዳን ገቡ። በዚህ ምክንያትም ሰራዊቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ በጣም ተመናመነ። ይህ በእንዲህ እያለ ግን የተወሰኑ ጥቂት ጓዶች የቋራ በረሃን ለቀን አንወጣም በሚል በቋራ በረሀ እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉ። እነዚህ ጓዶችም አንድ በአንድ በተለያ ጊዜ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋር ባደረጉዋቸው ውግያዎች በሙሉ በቋራ ተሰዉ። የኢህአሰ ፍጻሜም ከነዚህ ጓዶች መስወዋዕትንት በኋላ በ1985 ሆነ። ይህ የኢህአፓ/ሰ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋራ የደረገው ጦርንት ከመነሻው እስከ ፍጻሜው 1983 ግንቦት_1985 ያለው ጊዜ የጦርነት እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ ሊጻፉበት የሚገባ ሌላ አከባቢ ነው።

እንደኔ እምነት ጓድ አማኑኤል ማንጂስ በራስ አነሳሽነትና አፍላቂነት ይህን የዓሲምባ ፍቅርን በመጻፉ እሱ ራሱ የተሳተፈባቸው የድርጅቱ እንቅስቃሴዎችና የነበው ሁኔታን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲታወቅ አድርጓል፣ የሚያውቃቸው የነበሩ ሰማዕታት ታሪክ በህዝቡ ዘንድ እንዲታወቅና በተገቢ ደረጃ እንዲዘከሩ አስደርጓል። ለዚህ ስራውም ጓዱን እያመሰገንኩ ሌሎቻችንም የሱን አርአያነት በመከተል የየድርሻችን ለመወጣት እንዘጋጅ በማለት ይህን በዚሁ ቋሞቼ በዓሲምባ ፍቅር መጽሓፍ ደራሲ ላይ ወዳለኝ አስተያየት ልቀጥል።

**ለ. ጓድ ካሕሳይ/አማኑኤል ማንጁስ ጋር ያለን ትውውቅ፣**

የዓሲምባ ፍቅር ደራሲ ጓድ ካሕሳይ አብራሃ፣ የያነው ጓድ አማኑኤል ማንጁስንና እኔን ያስተዋወቀን ኢህአሰ ነው። በ1967 መጨረሻ የኢህአፓ ትጥቅ ትግል ለመጀመር በውጭ ሰልጥኖ ትግራይ/ዓሲምባ ከገባው ቡድን ወደ 8 የሚሆኑ አባላቱ ከድተው ወደ ዓዲግራት ከተማ እንደገቡ የትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድኑ ቁጥር ስለተመናመነ ይህን ቡድን በሰው ሃይል ለማጠናከር ዓዲ ኢሮብ/ዓሲመባ ወርደን ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ከጓዱ ጋራ የተገናኘውና የተዋወቅነው። ያኔ ትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን ለማጠናከር ሰው ሲፈለግ ጥሪውን ተቀብለን በአንድ ላይ ትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድንን የተቀላቀልን፣ አማኑኤል ማንጁስ፣ ይዕቢዮ፣ ሓረጎት፣ ነጻነት፣ አረጋይ፣ አታክልቲ፣ ጀማል፣ ጸሃየ፣ ነመራ፣ በርሄ፣ ሽፈራው፣ ወርቁ፣ ዓሊጋዝ፣ ግርማይ፣ አለሙና በየነ ጉራ ነበርን። ይህ ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ሜዳ በሰንገደ/ዓዲኢሮብ የመጀመሪያ ወታደራዊ ስልጠና ከውጭ ሰልጠነው በገቡ ጓዶች የወሰደ ቡድንም ነበር። ከኛ በፊት ደብሳይ ካሕሳይ፣ ደበሱ ካሕሳይ፣ ኩማኒት፣ ቢንያም፣ ወልዱ፣ ሓዲሽ ዛህላይ ታፈረ፣ ዓወት ከውጭ ሰልጥነው የገቡትን የተቀላቀሉ ጓዶች ናቸው። ከውጭ ሰልጥነው ትጥቅ ትግል ጀማሪ በሚል የሚታወቁት በትግል ስማቸው እኔ የማስታውሳቸው፣ ሮባ፣ ጅግሳ፣ ግደይ፣ ሀዋዝ፣ ዘላለም፣ ጸሀየ፣ ሀይለ ቀጭኑ፣ ግርማይ፣ ጌራ፣ ሮብለ ናቸው።

ለጓድ አማኑኤል ማንጁስ የሚል ቅጽል የተሰጠው በወቅቱ ትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡደኑን ከተቀላቀልን ከሁላችን በዕድሜ ያነሰ ስለነበረ ነበር። በታሊም/ስልጠና ቆይታችን ወቅት፣ ምንም እንኳን አማኑኤል ማንጁስ በዕድሜም ሆነ በትምህርት ከሁላችን ያነሰ የነበረ ቢሆንም በሚሰጠው ወታደራዊ ሆነ ፖለቲካዊ ስልጠና በንቃት ተሳታፊና የነበረውን ችግር/hardship በቆራጥነት ከማንኛችም ባልተናነሰ ደረጃ የተወጣ ጎበዝ ልጅ

ነበር። ሌላ ጓድ አማኑኤል ማንጂስ ያልተረዳውን ለመረዳት ከማንምኛችንም በላይ ጠያቂ፣ የማይመስለው ሃሳብ ከመጣ አጥብቆ ተከራካሪ፣ ሃሳቡን ምንም ሳይደብቅ/ሳይሸፋፍን በግልጽ አቅራቢና አዲስ ነገርን ቶሎ ለመቀበል የምችል ብሩህ አእምሮ የነበረው ጎበዝና ንቁ ልጅ መኖሩም በዛው በታዕልም ቆይታችን ወቅት ለመታዝብ ችያለሁ።

ወታደራዊ ስልጠናውን ጨርሰን በሁለት ጋንታ ተከፍለን ወደ እንቅስቃሴ እንደተሰማራንም ባጋጣሚ ጓድ አማኑኤል ማንጂስና እኔ ጓድ ጅግሳ በሚመራት ጋንታ አብረን ስለተመደብና እኔ ወደ ህዝብ የማደራጀት ስራ እስከምመደብ አብረን ስተንቀሳቀስን ይበልጥ እንዳውቀው ረድቶኛል። ጓድ አማኑኤል ማንጂስ በምናደረገው የነበረ ፈጣን እንቅስቃሴ ከብዙዎቻችን የተሻለ ጥንካሬ የነበረው ልጅ ነበር። ስለሆነም ለተለያ ተልእኮ ከሚመረጡትና ይህን ተልእኮ በሚገባ ከሚወጡም አንዱ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ባረፍንባቸው መንደሮች ሁሉ ከህዝቡ ጋር ቀርቦ በማነጋገርና የሰራዊቱን ዓላማ በማስረዳት ከጋንታዋ ውስጥ ከነበርን ሁሉ የበለጠ ኢንሼቲቭ የሚወስድና ተሳትፎ ሲያደርግ እንደነበረም አውቃለሁ። ጓድ አማኑኤል ማንጂስ ከነበረው አዲስ ነገሮችን ቶሎ የመቀበል ችሎታው የተነሳም ባጭር ጊዜ ውስጥ በኢሮብ ህዝብ የሚነገረውን የሳሆ ቋንቋ አጎላድፎም ቢሆን እስከመናገር ድረስ ሁሉ ደርሶም ነበር።

ሌላ መታወቅና መመስከር ያለበት ከውጭ ስልጥነው የገቡ የትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን ጓዶች ለጓድ አማኑኤል ማንጂስ ሆነ ለሌሎቻችን ከሀገር ቤቱ ለተቀላቀልናቸው አዲስ ወጣት አባላት የነበራቸው ፍቅር፣ አርአያነትና የተለየ እንክብካቤ ነው። እነዚህ ጓዶች ለኛ የነበራቸው ፍቅርና እንክብካቤ እኛ አዲሶቹ ደግሞ በጓዶቹ ላይ ልዩ እምነትና ፍቅር አሳድረን እንደ አርአያዎቻችን እንድናያቸው አድርጎን ነበር። በተለይ በወታደራዊ አመራር ማሰልጠንና አመራር አሰጣጥ ላይ እነ ጓድ ሮባ፣ ጓድ ጅግሳ፣ ጓድ ግደይ፣ጓድ ሮብለ ዓይነቶቹ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው መታወቅ አለበት። በመደበኛ ሰራዊት ደረጃ ከኢትዮጵያ ሰራዊት ሰልጠነው ከመጡት ወታደራዊ መሪዎች ወጭ ኢህአሰ ካፈራቸው የህይል ሆነ ጋንታ መሪዎች አብዛኛዎቹም የነዚህ ጓዶች ሰልጣኞች ወይም እነዚህ ጓዶች ያሰለጠኑዋቸው በተራቸው ያሰለጠኑዋቸው መሆናቸውም መታወቅ አለበት። ጓድ አማኑኤል ማንጂስም ሰራዊቱን እስከተወበት ጊዜ ድረስ ጥሩ አመራር ሲሰጡ ከነበሩ ብቃት ከነበራቸው ጋንታ መሪዎች አንዱ መኖሩ መታወቅ አለበት።

ሌላም ጓድ አማኑኤል ማንጂስ በመጽሓፉ ውስጥ ከጠቃቀሳቸው የወሎ፣ የበለሳ.... እንቅስቃሴዎች በተጨመሪ፣ በ1968 ኢህአሰ ገና በ4ና በ6 ጋንታ ደረጃ እያለ ሰፊውን የዓጋመ፣ ክልተ አውላዕሎና አንዳንድ የዓድዋ ገጠራማ አከባቢዎች ከጠላት ለማጽዳትና የሰራዊቱ መንቀሳቀሻ ወረዳዎች ለማድረግ በተደረገው ፈጣንና እልህ አስጨራሽ እንቅስቃሴ ሁሉ በብቃት ከተሳተፉ አንዱም ነው። ከዚህ በተጨማሪም በሳባ፣ ዓዲ አውዓለ፣ እንትጮ፣ ዓዲግራት፣ ውቅሮ፣ አጉላዕ፣ዓብዪ ዓዲ፣ የጭላ...ወዘተ.በተካሄዱና ሁሉም በድል ከተጠናቀቁት ወታደራዊ ኦፐረሽኖች በአብዛኛዎቹ የተሳተፈና ግዳጃቸውን በተገቢ ደረጃ ከተወጡ ጓዶችም አንዱ ነው።

## ሐ. በዓሲምባ ፍቅር መጽሓፍ ላይ ያለኝ አስተያየት፣

የዓሲምባ ፍቅር ላይ በመደገፍ እና በመቃወም የተለያዩ ትችቶች በተለያዩ ተቺዎች ቀርበው መጽሓፉን ከማንበቤ በፊት ሆነ መጽሓፉን ካነበብኩ በኋላም ተመልክቻለሁ። ከአንዳንድ ትችቶች ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው የዓሲምባ ፍቅር መጻፉና በተለይ በጓድ አማኑኤል ማንጂስ መጻፉ ብዙ የተዋጠላቸውና የወደዱት እንዳልሆነ ከሰነዘሩዋቸው ትችቶችና አንዳንዶችም በትችት ስም በደራሲውና በአንድ ብሄረሰብ አባላት ላይ ካነጣጠረው የውሸት ውንጀላቸው በቀላሉ መረዳት ችያለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ የዓሲምባ ፍቅር

ደራሲ የጀመረው በጎ ጅማሮ አድንቀው ቢስተካከል፣ ቢብራራ ያሉዋቸው አከባቢዎች ላይ አስተማሪ የሆነ ትክክለኛ ትችት የሰነዘሩም ለመመልከትም ችያለሁ።

የመጽሓፉን ይዘት ስንመለከት፣ ጓድ አማኑኤል በመጽሓፉ በመግቢያው ላይ እንደሚከተለው ይለናል፣ እጠቅሳለሁ፣ "ይህ የትግል ታሪክ በ1960ዎቹ መጨረሻና በ70ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ሲታገሉ ህይወታቸውን የሰዉ ጓዶቼ ታሪክ ነው። በበኩሌ እንዚህ ጓዶቼን መዘከር፣ እንዲሁም ቤተሰብና ዘመድ ወዳጆቻቸው እንዲኮሩባቸውና፣ ምን ዓይንት ልዩ ሰዎች እንደነበሩ እንዲያውቁላቸው፣ እስካሁን አውቀው ከሆነም ተጨማሪ ምስክርነቴ ያገን እንዲያጠነክርላቸው ለማድረግ መሞከር ግዴታየ ነው ብየ አምናለሁ። ስለአለፉት ውንደሞቻችንና እህቶቻችን መስዋዕትንትና እውነተኛ የወገን ፍቅር ሰሜት ቢያንስ የምናወቀውን ያህል በመንችለው መንገድ መመስከር አንዱ ሃላፊነታችን ነው።" ይላል።

ጓድ አማኑኤል ማንጁስ ይህን በመግቢያው ላይ ያስቀመጠውን ቃሉን በትረካው ውስጥ ጠብቆዋል? እሱ የሚያውቃቸውን የኢህአሰ ሰማዕታትን አንዱ ካንዱ ሳያበላልጥ፣ ዘር ሳይለይ ሰማዕታት ጓዶችን ታሪክ በትክክል በእኩልነት መስክሮዋል ወይ የሚለውን ስመለከት መልሱ ባጭሩ አዎን ነው። ይህን በቀላሉ እሱ በተሳተፈበት በወሎው የመጀመሪያ እንቅስቃሴ ስለተሰዉ ጓዶች፣ በበለሳ ስለተሰዉ ጓዶች፣ በውቅሮ ኦፐረሽን ስለተሰዉ ጓዶች ከጻፈው ትረካና ምስክርነቱ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

በኔ እይታ፣ የዓሲምባ ፍቅር ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ጓድ አማኑኤል ማንጁስ ራሱን ማእክል አድርጎ ወደ ኢህአሰ ከተቀላቀለበት ዕለት እስከ ሰራዊቱን ለቆ የወጣበት ዕለት ድረስ ያለውን እሱ ራሱ የተሳተፈባቸው የሰራዊቱ እንቅስቃሴዎችን፣ በዚህ የሰራዊቱ ቆይታው ወቅት እሱና ጓዶቹ ያሳለፉትን ውጣ ውረድን በምገርም የማስተወስ ችሎታው ከነቀናቶቹና ቦታዎቹ ጭምር በመጥቀስ ለሁልም በቀላሉ ሊገባ በሚችል ግሩም ቋንቋ ቀንጆ አድርጎ የተተረከበት መጽሓፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ጓድ አማኑኤል በመጽሓፉ በ1969 በሰራዊቱ ውስጥ ስለነበረው ምስቅልቅል የውስጥ ችግር፣ እርማት እንቅስቃሴ እየተባለ ስለሚጠራው ኢህአሰን ያሸመደመደ እንቅስቃሴ፣ በሰረዊቱ ውስጥ በአንጃ ስም ስለተከሰተው የውስጥ ችግር፣ በኢህአሰና ህወሓት መካከል ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ድረስ የነበረው ግኑኝነት፣ የ1970 የኢህአሰና የህወሓት ጦርነት ምን ይመስል እንደነበረ፣....ወዘተ. ብዙ ማለት ስችል በጣም በግርድፉ ብቻ በመጥቀስ፣ እነዚህን ውስብስብና አከራካሪ አከባቢዎች ለሚመለከታቸው በመተው እሱን ብቻ በሚመለከቱና በተራ አባል ደረጃ በሚታወቁ ጉዳዮች ዙሪያ ማተኩሩ የጓዱ ሀቀኝነት፣ ቅንነትና የኢህአሰ ትክክለኛ ታሪክ መጻፍ ከልብ የሚፈልግ ቅንና ግልጽ ጓድ መሆኑ በግልጽ አመላካች ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ሌላ በዓሲምባ ፍቅር አጻጻፍ ላይ የተገነዘብኩት አዲስ ክስተት እስከዛሬ በብዙ የፖለቲካ ድርጅት አባል የነበሩ/የሆኑ ጸሓፊዎች ከተለመደው ታሪክን ከፖለቲካ ጋራ እያደባለቁ መተረክ፣ ጥሩ ጥሩ ጎኑን ብቻ እያስቀመጡ የነበሩትን ስህተቶችና ድክመቶች እየደበቁ መተረክ በዓሲምባ ፍቅር ተሰብሮ ታሪክ ሚዛኑን ጠብቆ የተተረከበት ሁኔታም ተገንዝብያለሁ። ለምሳሌ ስለ ፍቅር ታሪኩ ሲተርክ እስከዛሬ ብዙ የድርጅቱ አባላት የነበርንም ሆነ አሁንም ነን የሚሉ ደፍረው የማይናገሩለት ግን በተግባር በጓዶችና በጓዲቶች መካከል ስለነበረው የፍቅር ግኑኝነት በተመለከተ ጓድ አማኑኤል በራሱና በጓዲት ድላይ መካከል የነበረው የፍቅር ግኑኝነት በሚገልጽበት ክፍል በቀላሉ መረዳት ችያለሁ።

ጓድ አማኑኤል ማንጁስ በሱና በጓዲት ድላይ መካከል የነበራቸው የፍቅራቸው ታሪክ በመተረኩ በአንዳንዶች እንደ ትምክህተኛ፣ በሌሎች ደግሞ የህንድ ፍልም ዓይንት ልበወለድ ተራኪ በሚል ተጥላልቶ ቢነቀፍም፣

ባንዳንዶቹ ደግሞ ዛሬ በህይወት የሌለች ራሷን መከላከል የማትችል ጓዲት በዚህ መልክ ማንሳትህ ተገቢ አይደለም በሚል ሂሳዊ አስተያየት ቢሰነዝርበትም እኔ ግን ስለነበራቸው የፍቅር ግኑኝነት በግልጽ መቀመጡ ታሪክ ነውና እየተጻፈ ያለው መጻፉ ተገቢም ትክክልም ነው እላለሁ። በሁለቱ ጓዶች መካከል በአንድ ወንድና ሴት ጓዲት መካከል ሊኖር ከሚገባው ጓዳዊ ግኑኝት በተጨማሪ ለየት ያለ የፍቅር ግኑኝነት እንደነበራቸው በመጽሓፉ ውስጥ እንደተጠቀሰው የሚያውቁ በህይወት ያሉ ጓዶች አሉ፣ እኔም ከነሱ አንደ ነኝ። ይህ የፍቅር ግኑኝነት በሁለቱ በጓድ አማኑኤልና በጓዲት ድላይ ብቻ ተወስኖ የቀረ ሳይሆን በብዙ ጓዶችና ጓዲቶች መካከልም የነበረ ግኑኝነት መሆኑም ምስጥር አይደለም። ስለሆነ የጓድ አማኑኤል ማንጁስና የጓዲት ድላይ ፍቅር እንደ አንድ ትልቅ ጉዳይ ተወስዶ አከራካሪ ለሆን የሚገባ አይመስለኝም።

ሌላም ለኔ አንዳንዶች እንደሚሉት ጓድ አማኑኤል ማንጁስ ከጓዲት ድላይ ጋር የነበረው የፍቅር ግኑኝት በመጽሓፉ ውስጥ በማካተቱና በመተረኩ ጓድት ድላይን ያሳነሳት ሳይሆን ይበልጥ ትክክለኛ ምንነቷና ለድርጅትና ለትግሉ የነበራት ፍቅር ከምንም በላይ መሆኑ በግልጽ የተመሰከረበት፣ ጓዲቷ ደግሞ ይበልጥ እንድትታወቅ፣ እንድትከበር፣ ጓዶቼዋና ቤተሰቦቹዋ ይበልጥ እንዲያውቁዋትና እንዲኮሩባት የሚያደርግ ሆኖ ነው የገኘሁት።ምክንያቱም ጓድ አማኑኤል ማንጁስ በመጽሓፉ ከጓዲት ድላይ ጋር የነበረው የፍቅር ግኑኝንት የገለጸበት አገላለጽና ጓዲቷ ስትለው የነበረ ብሎ ያስቀመጠው ልብ ብሎ ያነበበ ሰው ጓዲት ድላይ ለጓድ አማኑኤል ማንጁስ ፍቅር ቢኖራትም ከግል ፍላጎቷና ስሜቷ በፊት ትግሉን የምታስቀድም መሆኑዋን ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው በግልጽ ተጽፎ ማየት ይችላል። ስለሆነም ለኔ ጓዲት ዲላይ በዓሲምባ ፍቅር የተገለጸችበት አገላለጽ ለጓዲት ድላይ የነበረኝ ክብርና አድናቆት ጨመረልኝ እንጂ ፈጽሞ አልቀነሰብኝም። በመሆኑም ጓድ ካሕሳይ/አማኑኤል ማንጁስ በመጽሓፉ ጓዲት ድላይን የገለጸበት አገላለጽ ታሪክን በታሪክነቱ ከማስቀመጥ ውጭ ሌላ እንከን ያለበት ሆኖ አላገኘሁትም።

የጓድ አማኑኤል ማንጁስ የዓሲምባ ፍቅር በትግራይ፣ በጸለምት፣ በበለሳ፣ በወልቃይት፣ በአርማጭሆ፣ በቋራ፣ በጎጃም ...ወዘተ. ስለነበረው የኢህአሰ እንቅስቃሴ ታሪክ ለመጻፍ ለሚፈልጉ አዲስ መንገድ አሳይቷል፣ እንዲሁም ስለ ኢህአፓ/ሰ ታሪክ ከባለ ታሪኮቹ ለመስማትና ለማየት ለሚፈልግ የኢትዮድያ ህዝብ ደግሞ አሁን እየተጀመሩ ባሉ አዳዲስ ጅማሮዎች አንድ እርምጃ ጨምሯል ቢባል መጋነን አይሆንም። በኔ በኩል እስካሁን ካነበብኩዋቸው በኢህአፓ/ሰ አባላት ነበርን በሚሉ ከተጻፉ ጽሁፎች የዓሲምባ ፍቅር ታሪክ ሚዛኑ ጠብቆ የተጻፈበትና ድሮ የማውቀው የነበረ የጓዱ ሀቀኝነት፣ ግልጽነት፣ ላመነበት ዓላማ የነበረው ቆራጥነት በግልጽ የተመለከትኩበት መጽሓፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ስለሆነም ለወደፊቱ በኢህአፓ/ሰ ውስጥ ያሳለፉት ህይወታቸው በትክክል ለመተረክ የሚፈለጉ ጓዶች የሱን አርአያነት ቢከተሉ አይከፋም እላለሁ።

## መ. በትችት ስም በትግርኛ ተናጋሪ የሰራዊቱ አባላት ላይ ለተሰነዘሩ የውሸት የጅምላ ውንጀላዎች መልስ

ዕድሜ ለዘመኑ ተክኖሎጂ በጓድ አማኑኤል ማንጁስ በተጻፈው የዓሲምባ ፍቅር ላይ በመደገፍም ሆነ በመቃወም የተሰነዘሩ በርካታ ትችቶች በተለያዩ ድረገጾች ወጥተው ለማንበብ ችያለሁ። የአንድ ደራሲን ድርሰት ይዘት የደራሲው ሰብዕና ሳይነካ በጻፈው ታሪክ ይዘት መሰረት በመደገፍም ሆነ በመቃወም መተቸት የነበረ መቀጠልም ያለበት መሆኑ በሚገባ አምንበታለሁ። ከዚህ አንጻር በዓሲምባ ፍቅር መጽሓፍ ይዘት ላይ በመደገፍም ሆነ በመቃወም የተደረጉ አስተማሪ ትችቶችም ተገቢ ናቸው እላለሁ። ይህ በእንዲህ እያለ ከመጽሓፉ ይዘት ጋር ምንም ግኑኝነት የሌላቸው ደራሲውን አስታኮ በሰራዊቱ ውስጥ በነበሩ የአንድ ብሄረሰብ አባላት ላይ ያነጣጠሩ የውሸት የጅምላ ውንጀላዎች ግን ፈጽሞ ተገቢ አይደሉም መወገዝም ያለባቸው ናቸው። በተለይ እነወ/ሮ ጸዳለ አራት ሆነው፣ ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ በሚል ርእስ ባሰራጩት ባለ 5 ገጽ መጣጥፍና አቶ ሽፈራው ማን ያውራ የነበረ እንዲሉ ለቀባሪው አረዱት እንዳይሆን በሚል ርእስ በጻፈው

ባለ 5 ገጽ መጣጥፍ ይህ የውሸት የጅምላ ውንጀላ በግልጽ ማየት ይቻላል። እነዚህ በነወ/ሮ አጸደና በአቶ ሽፈራው በትግራዊያን ጓዶች ከሰነዘሩዋቸው የውሸት የጅምላ ውንጀላዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው የምላቸው የሚከተሉት ናቸው። እጠቅሳለሁ፣

- *"በመካከላችን እኛን መሰለው አብረውን በልተው፣ ጠጥተው የምንጠላውን የጠሉ መሰለው የልባቸውን ታማኝነት ለሌላ ድርጅት ያደረጉ ነበሩ፣"*
- *"የነዚህ ልባቸውን ለሌላ ድርጅት የሰጡ ሰዎች በኛ ውስጥ መሰግሰግ የድርጅቱን የውስጥ ትግል በዋናነት እንድናየው በማድረጋቸውና ቤዝ ሊቀይሩ ነው ብለው ሰራዊቱ ሳይሰማ ወያኔ እንድትሰማ በማድረግ በቂ ዝግጅት ሳይደረግ ጦርነት ውስጥ እንድንገባ ካደረጉን ምክንያቶች አንዱ ይመስለናል።"*
- *"ልንል የምንችለው በወያኔና በኢህአሰ መካከል በሚደረገው ጦርነት ወገን ለይቶ ላለመዋጋት የተወሰነ የታማኝ ታጋዮች ድጋፍ ነው ቢሉን ይገባናል፣ አለዚያም ተልእኮአችን ፈጽመናል ቢሉን ያስኬዳል።"*
- *"የወያኔ ሰርጎ ገብ ጓድ ተቢየዎች ኢህአሰ የሚያወጣውን የውግያ ፕላን ለወያኔ በማስተላለፍ ፣ ወያኔ ደግሞ ፕላኑን ለደርግ በማሳወቅ ደርግ ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅና እንድንመታ በማድረግ የጠላቴ ጠላት ወዳጅ ነው የሚለውን አገላለጽ በስራ ላይ አውለውታል።"*
- *"ብዙ የትግራይ ተወላጆች የቲፐኤለፍ እና የኢህአሰ ጦርነት በተፋፋመበት ጊዜ፣ ጦርነቱ ወደ ቤዝ በመጣበት ጊዜ ድርጅቱን ከድተዋል፣"*
- *"ለአማኑኤል መሰሎቹ መክዳት ዋና ምክንያት ሃቁ ጦርነቱ ወደ ቤዝ መቃረብና በጦርነቱን የወያኔ ድል መቀዳጀት ስለተገነዘቡ ነበር።"* ይሉናል።

ህወሓት/ኢህአዴግ በትረስልጣኑን ከያዘበት ከ1983 ጀምሮ እስከዛሬ ለ23 ዓመታት ህወሓት ለሚፈጽመው መረን የለቀቀ ግፍና ወንጀል የትግራይ ህዝብን ተጠያቂ ማድረግ፣ በህዝብና በድርጅት መካከል ያለው ልዩነት ለማየት አለመቻል/አለመፈለግ፣ የትግራይ ህዝብ እንዳለ በህወሓት ተጠቃሚ አድርጎ መፈረጅና መነጠል፣ በተለይ በዲያስፖራ በበርካታ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ የነበረ አሁንም ያለ አስተሳሰብና እምነት ነው ። ይህ ዓይነት አስተሳሰብና እምነት የኢህአፓ አባላት ነበርን/ነን በሚሉ ውገኖች ውስጥም የነበረና ያለ፣ ውስጥ ለውስጥ ሲታማና ስብሰለሰል የነበረ ቢሆንም ኢህአፓ እንደ ድርጅት ህወሓትን እና የትግራይ ህዝብን አንድ ላይ ፈርጆ ያየበት ጊዜ አልነበረም/የለም፣ በድርጅቱ ውስጥ የታገሉ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች አባላቱን በዘር በመከፋፈል ያገድን/የትግራይ ብሄረሰብ አባላትን በጅምላ ድሮም ሆነ ዛሬ እንደ ከሃዲዎችና የህወሓት ሰላዮች ነበሩ/ናቸው ብሎ የፈረጀበትና የከሰሰበት ጊዜና ሁኔታም አልነበረም/የለም። ኢህአፓ እንደ ድርጅት ይህን ያደርጋል የሚል እምነትም ፈጽሞ የለኝም።

ይህ በእንዲህ እያለ፣ ከላይ በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው የኢህአፓ/ሰ አባላት የነበሩ/የሆኑ እነወ/ሮ ጸዳለ በቡድን አቶ ሽፈራው ደግሞ በግሉ በመከታተል በዓሲምባ ፍቅር መጽሓፍ ትችት ስም በ1970 የትግራይ የኢህአሰና ህወሓት ጦርነት ወቅት ትግራዊያን በኢህአሰ ውስጥ ሆነው ለህወሓት ሰልለዋል፣ ሰራዊቱ በጠላት እንዲመታ አስደርገዋል፣ በጦርነቱ ወቅት ሰራዊቱን እየከዱ ሄደዋል በሚል በጅምላ ከባድ ክስ ከሰዋል። የኢህአፓ አባላት ነበርን/ነን በሚሉ ግለሰቦች ይህ ዓይነት አሰነዋሪ የጅምላ ውንጀላ በትግራዊያን ላይ በይፋ በድረገጾች በጽሁፍ ሲቀርብ ይህ የመጀመሪያ ይመስለኛል። የድርጅቱ አባላት ነን/ነበርን የመሉ ግለሰቦች ይህ ዓይነት ውንጀ በይፋ ሲበትኑ ድርጅቱ ይህን እያየ እንዳለየ በዝምታ ማለፍ አለበት ወይስ የለበትም የሚለው እንዳለ ሆኖ፣ በበኩሌ ግን ይህ ዓይነት የውሸት የቅጥፈት የጅምላ ውንጀላ በዝምታ መታለፍ የለበትም ባይ ነኝ። ስለዚህም እነ ወ/ሮ ጸዳለና አቶ ሺፈራው በትግራዊያን የኢህአሰ አባላት ላይ ከሰነዘሩዋቸው የጅምላ

የውሸት ውንጀላዎች መልስ ያስፈልጋቸዋል ያልኩዋቸውን እንደሚከተው በቀደም ተከተል መልስ እሰጥባቸዋለሁ።

1. **ትግራዊያን በኢህአሰ ውስጥ ሆነው ለህወሓት ሲሰልሉ ነበር ስለተባለው፣**

ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ ነውና በኢህአፓ/ሰ ወስጥ በተለይ በትጥቅ ትግሉ ትግራዊያን የነበራቸው ተሳትፎና ሚና ለመመስከር እችላለሁ ብዬ አምናለሁ። ለምን ብባል ትጥቅ ትግሉ በትግራይ ከተጀመረበት እስካበቃት ዕለት በቦታው ስለነበርኩ። በህወሓት የተጀመረውና ዛሬ ብዙ ኢትዮጵያዊን መርዞ ባለው በዘመኑ የጥላቻና የዘረኝነት ፖለቲካ የታወሩ እነ ወ/ሮ ጸዳለና አቶ ሽፈራው በኢህአሰ ወስጥ የነበሩ ትግራዊያንን በጅምላ በህወሓት ሰላይነት መፈረጃቸው እጅግ አሳምሞኛል፣ ለምን ቢባል በነወ/ሮ ጸዳለና በአቶ ሽፈራው በሰላይነት የተፈረጁ ጓዶችን በሚገባ ስለማውቃቸው፣ ዛሬ በኢህአፓ/ሰ ውስጥ የነበሩ ትግራዊያን ቀርቶ የራሱ የህወሓት አባላት የነበሩ ብዙ ሽዎች በህወሓት ተቃዋሚነት የቆሙ መሆናቸው በሚገባ ስለማውቅ ነው።

ጓድ ጸሀየ ሰለሞን በጻፈው አጭር የዓሲምባ ፍቅር መጽሓፍ ትችት ላይ እንዳስቀመጠው፣ አቢዮቱ በፈነዳበት በ1967 የደርግን ስርዓት በትጥቅ ትግል ለመታገል የትግራይ ወጣቶች ሶስት ምርጫዎች ነበሩዋቸው ማለት ኢህአሰ፣ ተሓህት እና ተሓት። ኢህአሰን ገና ከጅምሩ የተቀላቀሉ የትግራይ ወጣቶች በወቅቱ ተሓህት በኋላ ወደ ህወሓት ስሙን የቀየረው እና ተሓት ትጥቅ ትግል ልክ ኢህአሰ በጀመረበት ወቅት የጀመሩ መሆናቸውንና የት የት ቦታ እንደሚገኙም በሚገባ እያወቁ ተሓህትን እና ተሓትን ትተው ኢህአሰን ምርጫቸው አድርገው የተቀላቀሉት። ብዙ የትግራይ ወጣቶች የብሄር ጥያቄን በተገቢ መንገድ የሚፈታ ህብረብሄራዊ ትግል ላይ ከፍተኛ እምነት ስለነበራቸው ነበር ህብረ ብሄራዊ የሆነውን ኢህአሰን ከህወሓትና ተሓት የመረጡትና የኢህአሰ ትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን ትግራይ/ዓሲምባ ከገባበት ዕለት ጀምሮ በብዛት ይቀላቀሉት ጀመር። ስለሆነም ከ1967 የመጨረሻ አጋማሽ እከከ 1969 የመጀመሪያ አጋመሽ ባለው ጊዜ ኢህአሰ ከነበረው ሰራዊት ያለመጋነን ወደ 80%ቱ ትግራዊያን ነበሩ ማለት ይቻላል። የኢህአሰ አመራር ከነበረው አቅም አንጻር የሚቀበላቸው እየመረጠ በገደብ ስላደረገው ነው እንጂ ከትግራይ ከተሞች ሆነ ገጠር ሰራዊቱን ለመቀላቀል ወደ ዓዲ ኢሮብ ይጎርፉ የነበሩትን ወጣቶች ሁሉ ቢቀበል ኖሮ የትግራዊያን ቁጥር ከዚህም በላይ እጅግ ሊጨምር ይችል ነበር። ይህ ደግሞ በወቅቱ አመራር ላይ የነበሩ ጓዶች የሚያወቁት ሀቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ኢህአፓ/ሰ በራሱ ድክመትና የውስጥ ችግር ትግራይን ለቆ እስከሚወጣ በምስራቃዊ ትግራይ በገጠርም ሆነ በከተሞች ከህወሓት ይበልጥ እንደሆነ እንጅ ያነሰ ድጋፍና ተቀባይነት እንዳልነበረውም አፌን ሞልቼ መናገር እችላለሁ። ኢህአፓ/ሰ በውስጡ በተፈጠሩት ችግሮች፣ድክመትና በህወሓት በተደረገበት ግፊት ራሱ ትግራይን ለቆ ወጣ እንጂ አባለቱ ቀርቶ ራሱ የትግራይ ህዝብ ኢህአፓ/ሰን ፈጽሞ አልከዳውም።

ሌላም የህወሓት ሆነ የተሓት ዓላማ ምንነት በኢህአሰ ውስጥ የነበሩ ትግራዊያን ከማንም በላይ በግልጽ ያውቁ ነበር። በተለይ ህወሓት ከደደቢት/ሽረ ወደ ዓጋመ በመዝለቅ ተሓትን በዘገብላ እንዳለ መቶ ካጠፋ በኋላ፣ የትግራይ ነጻ ረፓብሊክ ለመመስረት እንደሚታገል የሚገልጽ ማኒፈስቶውን ዘርግቶ ኢህአሰን ከትግራይ ውጡልን ማለትን እንደጀመረ፣ የህወሓት ዓላማ ለሚቃወሙ ትግራዊያን ሁሉ በተለይ ደግሞ የኢህአፓ/ሰ አባላት ለነበሩ ኮራኹር አምሓራ/የአማራ ቡችሎች፣ ሽዋዊያን ተጋሩ በሚል በይፋ ፈርጆ መቀስቀስና ማጥላላት ከጀመረ በኋላ በኢህአሰ ውስጥ ለነበሩ ትግራዊያን የህወሓት ዓላማ በጣም ግልጽ ነበር። ስለሆነም በሰራዊቱ ውስጥ የነበሩ ትግራዊያን ኢህአፓ ህወሓት ገና በእንጭጩ እያለ አስፈላጊ እርምጃ እንዲወስድ በተከታታይ መወትወታቸውና ሰሚ እንዳጡ በወቅቱ በሰራዊቱ አመራር ላይ የነበሩ ጓዶች የሚያውቁት ሌላ ሀቅ ነው።

ሀቁ ይህ ሆኖ እያለ እነ ወ/ሮ ጸዳለ ትግራዊያን የኢ.ህአስ አባላትን በጅምላ በህወሓት ሰላይነት ፈርጀ መወንጀላቸው እጅግ አስገራሚም አሳዛኝም ነው። ትግራዊያን በትግራይ፣ በወሎ፣ በጸለምት፣ በወልቃይት፣ በበለሳ፣ በአርማጭሆ፣ በቋራ... በተደረጉ ትግሎች ሁሉ ከጓዶቻቸው ጋር ጎን ለጎን ታግለውና ተሰውተው፣ እያለ፣ በተለያየ በድርጅቱ ውስጥ በነበሩ ችግሮችና ድክመቶች ድርጅቱን ቢተወም አንድም ኢ.ህአሰን ከድቶ ወደ ህወሓት የሄደ ትግራዊ እንደሌለ እየታወቀ፣ ትግራዊያንን በህወሓት ሰላይነት መወንጀል ታሪክ ይቅር ሊባል የማይችል ከባድ ወንጀል ነው። ስለሆነም ለወደፊቱ ይህ ዓይነት ስህተት እንዳይደገም በሆነ ርእስ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ብዕር ከማንሳታችን በፊት ከስሜትና ከጥላቻ ራሳችንን ማጽዳት መልካም ነው እላለሁ።

2. <u>ልባቸውን ለሌላ ድርጅት የሰጡ ሰዎች በኛ ውስጥ መሰግሰግ የድርጅቱን የውስጥ ትግል በዋናነት እንድናየው በማድረጋቸውና</u> ቤዝ ሊቀይሩ ነው ብለው ሰራዊቱ ሳይሰማ ወያኔ እንድትሰማ በማድረግ በቂ ዝግጅት ሳይደረግ ጦርነት ውስጥ እንድንገባ ካደረጉን ምክንያቶች አንዱ ነው፣ ስለተባለው

እርግጥ ነው በ1969 አጋማሽ ጀምሮ በትግራይ በነበረው ኢ.ህአሰ ውስጥ ትልቅ የውጥ ችግር ነበር። የዚ.ህ የውስጥ ችግር ዋና ምክንያቶች ደግሞ በከተማ ደርግ በኢ.ህአፓ ላይ ያወጀው ቀይ ሽብርና በድርጅቱ አመራር ውስጥ የተፈጠረውና ወደ አባላትም በከተማ የተዛመተውና እርስ በርስ ያፋጀ የአንጃ ችግር ወደ ሰራዊቱም መዛመት ነበር። ደርግ በኢ.ህአፓ ላይ ቀይ ሽብር ዘመቻ አውጆ የኢ.ህአፓ አባላትን እንደ አውሬ ማደን እንደጀመረ፣ የድርጅቱ አመራር ውስጥ በወቅቱ ሀ እና ለ በሚል ሲገለጹ የነበሩ አመራር ጓዶች ከድርጅቱ አመራር ቢገለሉም የነሱ አስተሳሰብ የሚደግፋ አባላትና የቀረውን አመራር የሚደግፋ አባላት ሁሉ አንድ ላይ ተደባልቀው ነበር ወደ ትግራይ/ዓሲምባ በብዛት አንድ ጊዜ የመጡት። ስለሆነም ትግራይ የነበረው ኢ.ህአሰ የነዚ.ህ በከተሞች በደርግ ቀይ ሽብር መፈናፈኛ ያጡ አዲስ አባላት ማሸሻና ማሰባሰቢያ ማእከል ወደ መሆን ተቀየረ። በመሆኑም በወቅቱ ገና በመጀመሪያ የጎሪላ ዕድገቱ ደረጃ ላይ የነበረ አነስተኛ ሰራዊት ደረጃውን ጠብቆ ሊ.ያድ የምችልበት ዕድሉ መነመነ፣ በሰራዊቱ ውስጥ ስርዓት አለበኘነት፣ ለአንድ ጎሪላ ሀይል ህልውና ዋና መሳሪያ የሆነው ወታደራዊ ዲስፕልን ከሚገባ በላይ ላላ።

እነዚ.ህ አዲስ መጭዎች እንደዚ.ህ በብዛት ወደ ትግራይ ከመምጣታቸው በፊት የነበረው ትንሽ ሰራዊት ወታደራዊ ኮማንድ በሚል መጠሪያ የሚ.ታወቅ ጠንካራ፣ የጉሪላ ሃይልን ለመምራት ብቃት የነበረው አመራርና ውህደት የነበረው አነስተኛ የጎሪላ ሃይል ነበር። ይህ አነስተኛ ሃይል አንድ የጎሪላ ሃይል ሊ.ኖረው የሚ.ገባ ወታደራዊ ዲ.ስፕልንና አሰራር በሚ.ገባ የሚ.ያውቅና የሚ.ከተል ነበር። ይህ ጠንካራ ወታደራዊ ድስፕልንና ስነስርዓት ለአዲስ መጭዎቹ አልተዋጠላቸውም፣ በተጨማሪም እነሱ የጠበቁትና ዓሲ.ምባ ሆኖ የቆያቸው ፈጽመው ሊ.ጣጣሙ አልቻሉም። ስለ አንድ ጀማሪ የጎሪላ ሃይል በመጽሓፍ ከማንበብ ውጭ በተግባር ባልተፈተኑ አዲስ መጭዎች ባንድ ጊዜ መጥለቅለቅና በድርጅቱ በከተማ ተጀምሮ የነበረው የአንጃ ችግር ወደ ሰራዊቱም መዛመት ትልቅ ችግር አስከተለ።

ከነዚ.ህ አዲስ መጭዎች አብዛኛዎቹ በወቅቱ የሰራዊቱ አመራር ሲ.ከተለው የነበረ ጠንካራ ድስፕልንና ወታደራዊ አመራር አልወደዱትም። ስለሆነም በኮማንዱና በነባር አባላት ላይ ሰፊ የማጥላላት ዘመቻ ጀመሩ። የሰራዊቱ አመራር/ኮማንድን በአምባገነንነት አወገዙት፣ የቆዩ የሰራዊቱ አባላትም ጭፍን የኮማንዱ አሽከሮች፣ ያልተማሩ፣ ማርክሰዝም ሌኒ.ዝም ያላነበቡና ያላጤኑ በሚ.ል አወገዙዋቸው። በወቅቱ በሰራዊቱ ውስጥ ከነበራቸው ከፍተኛ ቁጥር አንጻር በዚ.ህ መልክ ከተወገዙት የድሮ አባላትም አብዛኛዎቹ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው ሰራወቱን የተቃላቀሉ ወጣት ትግራዊያን ነበሩ። እነዚ.ህ በአዲስ መጭዎች ክፉኛ የተወገዙትና በመጥፎ ዓይን መታየት የጀመሩት የቆዩ አባላት በአዲስ መጭዎች እንደዚ.ህ ዓይነት ዱላ ሲ.ሰነዘርባቸው ይከላከልልናል ብለው ያመኑት ድርጅት/በተለይ አመራሩ መውሰድ የሚ.ገባውን እርምጃ

ሳይወስድ ሲቀር፣ በጣም ሲያምኑዋቸውና በትክክል ሲመሩዋቸውና እንደ አርአያዎቻቸው ሲመለከቱዋቸው የነበሩ አመራራቸው እንደዛ ሲወገዝና ሲጨፈጨፍ፣ ዝም ብሎ የሚመለከት ድርጅት ምን ዓይነት ድርጅት ነው በሚል በድርጅቱ ላይ የነበራቸው እምነት እንዲላላ ሆነ። በተለይ ኢህአሰን እንዳለ ያሽመደመደው በአዲስ መጭዎች ሞብ ተመርቶ የተካሄደው እርማት እንቅስቃሴ በኋላ፣ ሰራዊቱ ብረት የታጠቀ የብዙሃን ድርጅት ዓይነት ሰራዊት ሆኖ ከቀረ በኋላ፣ ኢህአሰ እንደ አንድ ጉሪላ ህይል ወታደራዊ ድስፕልንና ስነስርዓቱን ይዞ ሊቀጥልና ሊያድግ የሚችል ሃይል ይሆናል በሚለው ላይ በርካታ ነባር አባላት ተስፋቸው መነመነ።

ሀቁ ይህ ሆኖ እያለ፣ ትግራዊያን ኢህአሰን ገና ከጅምሩ በመቀላቀል ያጠናከሩና ያሳደጉ ሆነው እያለ፣በስመ እርማት እንቅስቃሴ ከሰራዊቱ አመራርና ከሌሎች ነባር አባላት ጋራ አብረው የተወገዙና የተመቱ ሆነው እያለ፣ እነሱ ግንባር ቀደም የድርጅቱ የውስጥ ችግሩ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ ሆነው እያለ፣ ትግራዊያንን በትግራይ በኢህአሰ ውስጥ ለተከሰተው ውስጣዊ ችግር ተጠያቂ ለማድረግ መሞከር አህያውን ፈርቶ ዳውላውን ነው እላለሁ።

3. **ብዙ የትግራይ ተወላጆች የቲፕኤለፍና የኢህአሰ ጦርነት በተፋፋመበት ጊዜ፣ ጦርንቱ ወደ ቤዝ በመጣበት ጊዜ ከድተዋል፣ ለክህደታቸው ዋና ምክንያት ደግሞ ጦርንቱ ወደ ቤዝ መቃረብና በጦርነቱ የወያኔ ድል መቀዳጀት ስለተገነዘቡ ነበር፣** የሚለውን በተመለከተ

የህወሓት አመራር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅሞ ኢህአፓ/ሰን ከትግራይ ጠራርጎ ለማስወጣት ዓላማና ፍላጎት እንደነበረው ሁሉም የሚያወቀው የማይካድ ሃቅ ነው። የህወሓት አመራር ይህን ዓላማውን ለማሳካት ቀን ተሌሊት ይሰራ እንደነበረም ምንም ጥርጥር የለውም። ይህ የህወሓት አመራር ኢህአፓ/ሰን ከትግራይ የማባረር ዓላማ መኖሩ የኢህአፓ/ሰ አመራርም አባላትም ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ይህ እየታወቀ ግን የኢህአፓ/ሰ አመራር በህወሓት አመራር ለሚሰነዘርበት ጥቃት ለመከላከል ወይም አስቀድሞ አከባቢውን ለቆ ለመውጣት ምንም ዓይነት ዝግጅት አልነበረውም። በኢህአፓ/ሰ አመራር በኩል ለመከላከል ሆነ ለማጥቃት ምንም ዓይነት ዝግጅት አለመኖሩን የተገነዘበ የህወሓት አመራር ደግሞ በ1970 ኢህአፓ/ሰ ከፍተኛ የውጥ ችግር ውስጥ በተዘፈቀበት ወቅት፣ ይህን አጋጣሚን ተጠቅሞ ኢህአሰን ከትግራይ ጠራርጎ ለማስወጣት ተዘጋጅቶ የኢህአፓ/ሰ አመራር ፕላንና እርምጃዎች የሚፈትሽበት የተናጠል እርምጃዎች ከጥር ጀምሮ መውሰድ ጀመረ። በመጀመሪያ በተናጠል በእንትጬ፣ በብዘት እና በሳዕሲዕ ጓዶችን በተለያየ ጊዜ ገደለ። ቀጥሎ የካቲት መጨረሻ አከባቢ ሰበያ ላይ አንድ ቀን የፈጀ ግን ማንም ሰው ያለሞተበት የቶክስ ልውጥ በአንድ የህወሓት ህይልና በአንድ የኢህአሰ ህይል መካከል ተደረገ። ቀጥሎ በማይ መረቶ/ነበለት መጋቢት 5 1970 አንድ የኢህአሰ ሃይል ላይ ሁለት የህወሓት ህይሎች ከበባ በማድረግ ከሃይሏ በርካታ ጓዶች ተሰዉ፣ ብዙዎችም ቆሰሉ። ከሞት የተረፉት ቁስለኞቻቸውን ይዘው ወደ ቤዝ/ዓዲኢሮብ ተመለሱ። ይህ ሁሉ እየሆነ በኢህአሰ አመራር በኩል ምንም ዝግጅት አልነበረም። ቀጥሎ መጋቢት 19 1970 ብዘት ላይ ሁለት የኢህአሰ ሃይሎች በህወሓት በኩልም ሁለት ሃይሎች የተሳተፉበት ቀኑን ሙሉ የፈጀ ከባድ ውግያ ተካሄደ። ወደ ምሽት ላይ በሁለቱም በኩል ብዙ አባላት ሙትና ቁስለኛ ሆነው በሁለቱም በኩል የነበሩ ሃይሎች ተዳከሙ። በህወሓት በኩል ለተዳከሙ ሃይሎች እርዳታ ሲደርስላቸው በኢህአሰ በኩል ግን ምንም እርዳታ አልደረሰም። እነዛ የተዳከሙ ሁለቱ ሃይሎች ምንም እርዳታ ሳያገኙ ችግሩን በራሳቸው ብቻ እንዲጋፈጡት ተተወ። ከሁለቱ ሃይሎች በህይወት የተረፉ ጓዶች ቁስለኞቻቸውን ይዘው ወደ ቤዝ/ዓዲ ኢሮብ ተመለሱ።

የህወሓት አመራር የጀመረውን ኢህአፓ/ሰን ከትግራይ ጠራራርጎ የማስወጣት ዓላማውን ለመፈጸም ሚያዚያ 26 ሰራዊቱን በሚገባ አሰባስቦ ከዓዲግራት ወደ አስመራ የሚወስደውን ዋና መንገድ ተሻግሮ በግዕተሎና በሰበያ በኩል ወደ ቤዝ/ዓዲ ኢሮብ ተንቀሳቀሰ። የህወሓት ወደ ቤዝ እየመጣ መሆኑ ያወቀ የኢህአፓ/ሰ

አመራር በቀጥታ መያዝ ከማይቻለው ንብረት የተቻለው ያህል እንዲቀበር፣ የተቀረው በሙሉ እንዲቃጠል፣ ቤዝ የነበሩ ክፍልታት ሁሉ ወደ እንዳልገዳ እንዲያፈገፍጉ፣ በሰንገደ የነበረው ስለጠናና ክፍልታትም ወደ እንዳልገዳ እንዲንቀሳቀሱ፣ ክፍልታት በሙሉ ቤዝ ለቀው እስከሚወጡ ደግሞ ሃይሎች የመከላከል ውግያ እያደረጉ ወደ እንዳልገዳ እንዲያፈገፍጉ ትእዛዝ አስተልልፎ እንቅስቃሴው ተጀመረ። ሚያዚያ 28 ህወሓት ወደ ዓዲ ኢሮብ በአዎና በኢስላምቶዳ በኩል መግባት ጀመረ። ኢህአፓ/ሰም መቅበር የሚቻለውን ንብረት ቀብሮ፣ የሚቃጠለውንም አቃጥሎ ቤዝ የነበሩ ክፍልታትን በዓይጋና ወርዓትለ በኩል እንዲያፈገፍጉ አሰደረገ። ሚያዚያ 30 ህወሓት ወደ ዓይጋ ዘለቀ፣ ኢህአፓ/ሰም አንዳለ ዓዲ ኢሮብ የነበውን ሀይሉን አሰባስቦ ጠቅልሎ እንዳልገዳ ገባ። ግንቦት 1 ህወሓት ወደ እንዳልገዳ ዘለቀ፣ ኢህአፓ/ሰ ደግሞ ጠቅልሎ ወደ ሺመዛና/ኤርትራ ገባ። ህወሓትም መከታ/የእንዳልገዳ የጠረፍ መንደር ደርሶ መከታ ላይ ቆመ። ህወሓት መከታ ላይ የቆመውም ሽመዛና የጀብሃ ነጻ የወጣ የኤርትራ መሬት መሆኑ ህወሓት ስለሚያውቅና ወደ ሽመዛና ዘልቆ ኢህአሰን እወጋለሁ ቢል ከጀብሃ ጋር እንደሚጋጭ ስላወቀ ነበር መከታ ላይ የቆመው። ኢህአፓ/ሰም ሽመዛና ላይ እጁን ለጀብሃ ሰጠ።

ሀቁ ከላይ የተዘረዘረው ሆኖ እያለ፣ የኢህአፓ/ሰ አመራር የህወሓት ወረራ ለመከላከል ምንም ዕቅድ እንዳልነበረው እየታወቀ፣ የኢህአሰ ሃይሎች ከህወሓት ሃይሎች ጋር ውግያ ያካሄዱት ሶስት ጊዜ ማለት ሰበያ፣ ማይመረቶ/ነበለትና ብዘት ብቻ መሆኑ እየታወቀ፣ በተለይ የኢህፓ/ሰ ዋና ቤዝ በነበረው ዓዲ ኢሮብ ከሽሽት ውጭ ምንም ዓይነት ውግያ እንዳልተካሄደ እየታወቀ አቶ ሽፈራው ጠርንቱ በተፋፋመበትና ወደ ቤዝ በተጠጋበት ጊዜ ብዙ የትግራይ ተወላጆች ከድተዋል ሊለን ይፈልጋል። ይህ ፈጽሞ ነጭ ውሸት ነው። በርግጥ ብዙ ጓዶች ኢህአፓ/ሰ የሚቃጠለውን ንብረት አቃጥሎ ጠቅልሎ ወደ ኤርትራ እየሸሸ መሆኑ ካረጋገጡ በኋላ በተለይ ትግራዊያን ሰራዊቱን እየተዉ በየአቅጣጫው ተበታትነዋል። ግማሹ ለጀብሀ እጁን በመስጠት ወደ ወጭ ተሰዷል፣ ቁጥራቸው የማይናቅ ወደ ዓዲ ኢሮብ ተመልሰዋል። ወደ ዓዲ ኢሮብ ከተመለሱት የተወሰኑት ከህወሓት ጋር በተለያየ ጊዜ ባደረጉዋቸው መታኮሶች ተሰውተዋለ። የተቀሩት በዓዲ ኢሮብ መቆየት የማችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር እጃቸውን ለደርግ ሰጥተው፣ በደርግ ስር በሚልሻነት ተደራጅው ከህወሓት ጋር በተለያየ ጊዜ በተደረጉ ጠርነቶች ተሰውተዋል።

## ማጠቃለያ፣

የኢህአፓ ሰራዊት ኢህአሰ ለምን ፈረሰ? የሚለው ከባድና ውስብስብ ጥያቄ ለመመለስ መንስኤዎቹን ሁለገብ በሆነና ከስሜት ጉም በጠራ ዐይን መመልከትና ማጤንን ይጠይቃል። ይህን ለማድረግ ይረዳ እንደሆነ በሚል ለናሙና ያህል አንድአንድ የሰራዊቱ ታሪካዊ ክንዋኔዎችና ለሰራዊቱ ውድቀት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸው የውስጥና የውጭ ችግሮችን በአቅሜ ደረጃ ለመጠቃቀስ ሞክሬያለሁ።

በሌላ በኩል ይህን ሀቅ አውቆ በመዘንጋት ወይም በግል ፍላጎትና በጠባብ የፖለቲካ አስተሳሰብ የተበከሉ አንዳንድ ግለሰቦች ኢህአሰ የፈረሰው የትግራይ ተወላጅ ጓዶች ውስጥ ለውስጥ ድርጅቱን እየቦረቦሩ ስላዳከሙት ወይም ደግሞ የትግራይ ህዝብ ሰራዊቱን ስላልተቀበለውና ስላላቀፈው ነው የሚል እንደምታ ያለው አቀራረብ ተመልክቻለሁ። ይህ ፈጽሞ ከኡነት የራቀና ሆን ተብሎ ታሪክን ለማጉደፍ የሚሰነዘር ተንኮልና ሴራ ነው ማለት እደፍራለሁ።

እንዲያውም እኔ በተዘዋወርኩባቸው የትግራይ ክፍሎች በሙሉ የትግራይ ህዝብ ለኢህአሰ ዓላማ ይሰጠው የነበረ ድጋፍና ተሳትፎ ለህወሓት ይሰጠው ከነበረው ድጋፍ የበልጠ እንጅ ያነሰ አልነበረም። ለምን ቢባል የትግራይ ህዝብ ታሪኩም እንደሚያስረዳው በኢትዮድያ ሉዓላዊነትና አንድነት ከልብ የሚያምን፣ ለሀገሩና

ለባንደራው/አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ ከፍተኛ ፍቅር ያለውና የሀገሩ አንድነት ለማስከበርም ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለ፣ የህወሓት የመገንጠል ዓላማ ገና ከጥዋቱ ፈጽሞ ያልተዋጠለትና ዐቅም አጥቶ ነው እንጂ የኤርትራም መገንጠል የማይቀበል ኩሩ ኢትዮጵያዊ ህዝብ ነው።

የትግራይ ህዝብ ኢህአሰና ህወሓት በጋራ በተንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች ሲያነሳውና ሲጠይቀው የነበረ ለምን አንድ አትሆኑም፣ ለምን በጋራ የጋራ ጠላታችሁ የሆነውን ደርግ በጋራ አትታገሉም፣ ለምን አንድ ላይ ሆናችሁ አታታግሉንም እያለ ነበር። እናንተ ስትጣሉ የሚጠቀመውና የሚጠናከረው የጋራ ጠላታችሁ የሆነው ደርግ ስለሆነ እባካችሁ ተዉ ተስማሙ እያለ ነበር ዘወትር የሚማጸነው። ይህ ደግሞ ዛሬ በዕድል በህይወት የተረፉ ሀቀኛ የኢህአሰ ሆነ የህወሓት አባላት ሊመሰክሩት የምችሉት ሀቅ ነው ብዬ እገምታለሁ።

ዛሬ ላይ ቆሜ ትናንትን ወደ ኋላ መልስ ብዬ ሳስበው እጅግ የሚያሳዝነኝ ነገር ቢኖር፣ የህዝቡን ምክርና ልመና ጆሮ ዳብ ተብሎ ለስልጣን ሽኩቻ በሁለቱ ህይሎች መካከል በተደረገው ጦርነት ከሁለቱም ወገን ለሀገራቸውና ለህዝባቸው ከፍተኛ ፍቅርና ህልም የነበራቸው፣ በርካታ ቆራጥ ታጋዮች ውድ ህይወታቸውን በለጋ ዕድሜያቸው እንዲከፍሉ መደረጉ ነው። ይህ አሳዛኝ ክስተት በገጠር በኢህአሰና በህወሓት ብቻ ተገድቦ የቀረ ሳይሆን በከተሞችም አእላፍ ወጣቶች በቡድን በኢህአፓና በመኤሶን.... ተቧድነው እርስ በርስ የተፋጁበትና አንድ ትውልድ እንዲመተር ያስደረገ አሳፋሪ፣ አሳዛኝና መራራ ታሪካችን ነው።

ይህ የመጠፋፋትና የኔ መንገድ ብቻ ሀቀኛ ነው ፖለቲካ ታሪካችን አሁን ቆሟል፣ ለወደፊት አይደገምም ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገር የሚያስችል ሁኔታ ላይ ዛሬ እንገኛለን ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር አይመስለኝም እና በሁላችን የ60ዎቹ ትውልድ አባላት ቢታሰብበት መልካም ይመስለኛል። ይህን እኔ ብቻ ሀቀኛ ነን ሌላው ሁሉ ስተተኛ ነው የሚለውን የፖለቲካ አካሄድና አስተሳሰብ አቁመን አዲስ አስተሳሰብና ሁሉንም ዓይነት ፖለቲካ ሊቀበል የምችል ስርዓት ለማምጣት ገና ብዙ ትግልና ረጅም ጉዞ የሚጠይቅ ይመስለኛል።

ያለፈው መራራ ታሪካችን ዘግተን ለወደፊት እንዳይደገም ለማድረግ ከልብ ከፈለግን ደግሞ መፍትሄ ሊሆን የምችለው ያለፈው ታሪክ በፖለቲካና በግል ስሜት ሳይበረዝ በታሪክነቱ በሀቀኝነትና በቆራጥነት ለአዲሱ ትውልድ ለማቅረብ ከተቻለና ከዚህም መራራ ታሪካችን ትምህርት ለመቅሰም ከበቃን ብቻ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

ከመጠፋፋት ፖለቲካ ወጥተን ሁላችን ተክባብረን በጋራ በሰላም የምንኖርባት አንዲት የጋራ ዴሞክራሲያዊት ሀገር ለመድረስ ገና ብዙ ጉዞ መጓዝ አለብን። አሁን እያንዳንዳችን ይዘነው ያለነው አስተሳሰብና አካሄድ ለመቀየር በመካከላችን መካሄድ ያለበት ከባድና ፈታኝ ትግል ገና አልተጀመረም። የጋራ ሀገር ለመመስረት አንዳችን አንዳችንን ሳናገል በጥይት ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ በጥልቀት በመቻቻል፣ በመደማመጥና ሰጥቶ ለመቀበል በመጀጋጀት መወያየትና መመራመር የግድ ነው።

ኢትዮጵያ በነጻነቷ ኮርታ፣ በተለያዩ ህዝቦቿ ደምቃና አሸብርቃ፣ ድህንትና ኋላቀርንት አሸንፋ፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተጎናጽፋ፣ በሰላምና በአንድንት ለዘለዓለም ትኑር!!!

በየነ/ጉራ ገብራይ

ጥር 2006 (January 2014)